በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ
እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና ወርሃዊ

# የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 21-31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

## እንዲሁም 1-10፤ 11-20 ኖቬምበር 2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ - 1 -

ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች ........ - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ........ - 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 5 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 5 -

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ.- 6 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 6 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ........ - 7 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 8 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 9 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 10 -

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 10 -




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት የኦክቶበር ሶስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት ከመጠናከሩ ጋር ተያይዞ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ዝናብ ነበራቸው፡፡ እንዲሁም ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች አንጻራዊ መጠናከር በማሣየታቸው ምክንያት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት የዝናቡ መጠንና ስርጭትም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከበድ ያለ እና የተስፋፋ ገጽታ ነበረው። በመሆኑም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው አከባቢዎች ለመጥቀስ ያህልም በአርባምንጭ 31.8፣ በባህርዳር 61.4፣ በጎዴ 30.8፣ በጅማ 32.6፣ በአማን 49.6፣ በአንገር ጉቲን 30.6 እና 54.0፣ በአርጆ 34.2፣ በአፅቢ 33.4፣ በቡሂ 78.8፣ በቡለን 30.4፣ በቻግኒ 31.2፣ በጭራ 30.9፣ በዳንግላ 48.2፣ በደብረ ታቦር 40.7፣ በፉኚዶ 49.1፣ በጋቲራ 31.6፣ በሀረሪ 30.6፣ በሆሳዕና 40.7 እና 42.2፣ በሊሙ ገነት 35.5፣ በማሻ 30.6፣ በነፋስ መውጪያ 36.3፣ በፓዌ 34.3፣ በሸርቆሌ 48.6፣ በሽሬ 30.2፣ በባቱ 33.2፣ በሻላቦ 65.0፣ በአለም ተፈሪ 42.4፣ በገርቦ 30.4፣ በአዋሮ 34.2 እንዲሁም በአዋሮ መልካ 37.6 በሚ.ሜ. ይጠቀሳሉ (ምስል 1) ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ምስል፡1 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበል፣ የነጎብ፣ የቆራሂ እና የዶሎ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከ51-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን ባሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ፤ እንዲሁም የሲቲ፣ የፋፈን፣ የኤረር፣ የጃረር ዞኖች ከ16-50 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው:: በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ51-160 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡

በሌላ በኩል የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት አከባቢዎች ማለትም በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅና በደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የዋግህምራ፣ የሰሜን ወሎ፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ የማሂ፣ አውሲ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፤ በተጨማሪም ከሶማሌ ክልል የሲቲ ዞን፤ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ16-50 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-6 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን የደቡብ ወሎ፣ የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ) እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ የምስራቅ፣ የምዕራብ የደቡብ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ ከ6-30 ሚ.ሜ ከ4 ላነሱ ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፤ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ፤ ከሶማሌ ክልል የሊበን፣ የዳዋ፣ አፍዴር፣ የሸበሌ፣ የነጎብ፣ የቆራሄ፣ የዶሎ ዞኖች የሲቲ፣ የፋፈን፣ የኤረር፣ የጃረር፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሊ እና ባስኬቶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ የነበሩት የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም፤ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት በቦረናና በጉጂ ዞኖች ለተዘሩ የበጋ ሰብሎች ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን፤ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ገንቢ ሚና ነበረው። በአንጻሩም ከክረምት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ በነበሩት በደቡብ ምዕራብ አጋማሽ የመኸር አብቃይ አከባቢዎች የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍርፍሬዎች እንዲሁም በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ለተተከሉ የተለያዩ የዛፍ ችግኞች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸዉ ከማድረግ አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ እንዲሁም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ እና ስንዴ በመሳሰሉ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው አዋሽ፣ የታችኛውና የመካከለኛው አባይ እንዲሁም የመካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው ተከዜ፣ በጥቂት የታችኛው አዋሽ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለገፀ ምድር እና ለከርሰ ምድር የዉሃ አቅም መጨመር አዎንታዊ ጎን እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ በታችኛው አዋሽ እና ታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት



ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የዝናቡ መጠንና ስርጭት ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

በሚቀጥሉት ቀናት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች እና የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ይኖረዋል (ካርታ 6)፡፡ እንዲሁም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በምዕራብና ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ዳዉሮ፤ ማጅንግ ዞን፤ እና ላይ በጥቂት ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ወላይታ፣ ኮንሶ፣ በጌዲኦ፣ ባስኬቶ በጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፤ አሌ፤ በአማሮ እና ቡርጂ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበል፣ ኖጎብ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ ፋፋን፣ ኤረር እና ጃረር፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ እንዲሁም ከክረምት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ ባሉት አከባቢዎች ማለትም በምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ የኢታንግ ልዩ ዞን፣




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ኑዌር እና አኝዋክ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከአማራ ክልል ምዕራብ፤ ሰሜን፣ ማዕከላዊና ደቡብ ጎንደር፤ ምስራቅ፤ ምዕራብ እና ሰሜን ጎጃም፤ አዊ ዞኖች እና ባህርዳር ዙሪያ፤ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፤ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ፤የምዕራብ፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅና ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፋንቲ፤ ማሂ፣ ሃሪ፣ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ አዲስ አበባ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል(ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1-10, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1-10, 2024
የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተመሳሳይ ሁኔታም እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ  የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትት ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 8)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)፡፡

Total Rainfall (mm) 11-20,Nov 2024




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የሚኖረው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፣ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸዉ ከማድረግ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ለተዘሩና ለሚዘሩ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላ በኩል በተለይም ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ቅድም ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ከመኖሩ ጋር ተዳምሮ በመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባርት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል አርሶ አደሮችም ሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ልዩ ትኩረት በመስጠት የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ለማከናወን አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመርያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛዉ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ የታችኛው አባይ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ የሚያገኙ ሲሆን፤ በተጨማሪም በመካከለኛው እና በታችኛው ተከዜ እንዲሁም አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ያገኛሉ፡፡ የሚኖረው የእርጥበት ሁኔታም የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር የዉሃ ሃብትን ግብዓት በማሻሻል ለዘላቂ የውሃ ሀብት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ የላይኛው ተከዜ እንዲሁም የታችኛው አዋሽ ምስራቃዊ ክፍል ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡**



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et